PANORAMA # 10

## የትዝብት አድማስ

ጥር 16 2009

## ጎራው እየለየ ፥ማንነት እየታየ

*በወቅቱ የሀገራችን የፖለቲካ መልከአ-ምድር የተከሰተውን፥ የኃይሎችን አሰላለፍ በሚገባ ለሚከታተል ዜጋ፥ በሂደት ግልፅ እየሆነ የመጣውን ተጨባጭ ሁኔታ መታዘብ አያስቸግረውም:: " ወያኔን ተፃርረን ቆመን ነበርን " የሚሉ ክፍሎች በተለያዩ ምክንያቶች የየራሳቸውን ግምጋሜ በማካሄድ የአቋም ለውጥና መሸጋሸግ በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ከዚህም በመነሳት፣ የፖለቲካ ብልጦችና ከጊዜው ጋር ሊራመዱ የሚችሉ ወገኖች የሚል ስያሜን እናገኛለን በማለት፥ አዲስ የፖቲካ ለምድ ለማጥለቅ እየሞከሩ ናቸው:: መለስ ዜናዊ፥ በአደባባይ ብጣሽ ጨርቅ ነች ብሎ ያዋረዳትን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ፥ ለፖለቲካ ዘማዊነት እንዲጠቅመው ሲል በስብሰባ ላይ በመልበሱ ምክንያት፥ በአንድ ቀን ዠምበር ለኢትዮጵያ ጥቅም እንደቆመ አድርገው ደመድመዋል:: ከዚህም አስቂኝ ከንቱ ግንዛቤ በመነሳትም፥ የሀገራችን የፖለቲካ ሂደት መልካም ጅማሮና አውንታዊ አቅጣጫ እንደሚከተል ተደርጎ እየተቆጠረ ነው:: ወያኔን ወያኔ አትበሉት:: መለስ ዜናዊንም፥ "ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር" በሏቸው የሚባል ማኅሌተ-ማኅሌት እያሰሙ ይገኛሉ:: ይህ ሁሉ የአቋም ሽግሽግና የአሰላለፍ ረድፍ አለዋወጥ፥ ዓላማው አንድ ብቻ ነው:: "ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ ዥግራ ነች" ለማለት የሚደረግ ከአንድ ጎራ ሰልፍ ወደ ሌላው ጎራ ለመገልበጥ እንዲያመች የመሰናዶ ቅድመ -ዝግጅት ሽር-ጉድ ነው:: " አቅጣጫ ለመለወጥ፥ በአንድ ተራ ግባ!" ተብለው በወያኔ የዓጋዚያን ጦር አለቃ/ አሰልጣኝ የታዘዙ ይመስል፥ ሰልፍ ለማሳመር በመሽቀዳደም ላይ ይገኛሉ::*

*ይህ ሽር ጎድ፥ ከሁለት ዓመቶች በኋላ ለሚደረገው የወያኔ ምርጫ ተሳትፎ እንዲረዳ የቅድሚያ የሰልፍ ልምምድ የሚረዳ ጥርጊያ መንገድ ለመክፈት/ ለማስከፈት እንደሚሆን ለማንም የፖለቲካ ታዛቢ የተሰወረ አይሆንም:: ለዚህ ዶሮ ጭራ ለምታወጣው የመሰሪነት ቅሌት እንዲረዳቸውም፥ ሀገሪቱ ሰላም ያሻታል፥ ኢሕአዴግ ብዙ ማሻሻል በማድረግ ላይ ነው:: አክራሪ መሆን አያስፈልግም:: በጦር ነካሽነት መፈረጅን አንፈልግም:: የሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ፥ የአካባቢያችንና የዓለም አቀፍ ሁኔታዎች በሠላም ብቻ ከመታገል በቀር፥ ሌሎች የትግል ምርጫዎች ለመፈለግ አያመቹንም:: ጊዜያችን እንዲሁ በከንቱ እያለፈ ነው፥የሚሉና የመሳሰሉት ትጥቅ አስፈቺ ትርኪ-ምርኪዎች ናቸው::*

*በማነኛውም የፖለቲካ ትግል ሂደት እንዲሁም በማነኛው ጊዜና አጋጣሚ፥*

*የአቋም ለውጥ ማድረግና ሰልፍንም መለዋወጥም ይሁን፥ ዕምነትንም መቀየር፥ ያልተለመደ ባመለሆኑ፥ እንደ አዲስ ክስተት ተቆጥሮ ማንንም የሚያስገርም መሆን እንደሌለበት እንረዳለን። የትግሉን ጎራ እየለቀቁ ለመሄዳቸው የሚረዳ ማጠየቂያ ለማግኘት ሲባል፥ በዓላማቸው በመጽናት ወያኔን አምርረው የሚታገሉትን ክፍሎች  እንደ ገፀ-በረከት ለመጠቀም መሞከር ግን መጃጃል ካልሆነ በስተቀር የሚያመጣው ፋይዳ አይኖርም። ቆራጡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በመራራ ትግሉ ወያኔን  በማንበርከክ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ይገነባል እንጅ፥ ለዘረኞች አገዛዝ አይንበረከክም። ይህ አባባል፥ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታና ለሞራል ግንባታ  የሚነገር ነባቢት  ሳይሆን፥ በታሪክ የተመሰከረ የቆራጥ ታጋይና የነአይበገሬ የቃል ኪዳን ድምፅ ነው። ውጤቱም ወደፊት ይታያል።*

*ምንም ምን ቢሆን በአሁኑ ወቅት፥ የተቃዋሚ ጎራውን ሁኔታና አቋም በሚመለከት፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግለፅ የሆነለት ሀቅ አለ። ይኸውም እስካሁን ድረስ ኅብረት ለመፍጠር የተሞከሩት ሙከራዎች ሁሉ የተጠበቀውን ያህል ውጤት ያላስገኙ መሆናቸውን ነው።  በመሆኑም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለምንስ ውጤት አላስገኙም ብሎ በመጠየቅ ምክንያቶቹን ለመፈለግ ብዙ እንደማያስጨንቀውም ከተረዳ ቆይቷል። ይህንን በሚመለከትም ከተቃዋሚው ጎራ ብዙ እንደማይጠብቅ ሳይገነዘበው የሚቀር አይመስልም። በጣም ሊገረም የሚችለው ግን በተለያዩ ምክንያቶች፥ ድርጅት እያዳከሙ፥ ነባሩን ድርጅቶችንም እያፈረሱ፥ የተፈጠሩትንም፥ የተለያዩ ኅብረቶችንና ስብስቦችን እየለቀቁ፥ ለጊዚያዊም ቢሆን፥ የትግሉን ሂደት እያቃወሱ፥ መላ ቅጡ ወደጠፋበት አቅጣጫ ሲንከራተቱ መታዘቡን ነው። በእኛ ዕምነት፥ይህ ተሰፋ የመቁረጡና  ቅጥ አምባሩ የጨለመበት ድርጊትና ባኅርይ እንዳለ ሆኖ፥ አሁንም የሀገራችንን ሁለገብና ስር የሰደደ ችግር ለመፍታት የሁሉንም ጥረትና ትግል የሚያስፈልግ መሆኑን ነው።*

*ይህንን ሀቅ ሳይረዱ፥ እንዲያው በደፈናው፥ አንድ ወይም ጥቂት ክፍሎች ብቻ ተጠራርተው የሀገሪቱን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች እናስወግዳለን ብሎ  የአቋምና የጎራ መሸጋሸግ መፍጨርጨር፥ ከምኞት ባሻገር የሚያስመዘግበው የረባ ውጤት አይኖርም። ምናልባት ተደጋግሞ ተደጋግሞ ሲነገር የሚያሰለች መስሎ ሊታይ ይችል እንደሁ ባናውቅም፥ የሀገሪቱን ስር የሰደዱ ችግሮች ለመፍታት፥ በግድ የሁሉንም ጥረትና ትብብር የሚያስፈልግ መሆኑን አጥብቀን እናምንበታለን። ይህ ዕምነታችን የተመሠረተው በምኞትና በቀቢፀ-ተሰፋ ላይ ሳይሆን፥ በዕርግጥ ለሀገራችን ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ዋስትና  ሊያስገኝ የሚችል ተስፋ ስለሚሰጥ ነው።  በመሆኑም፥ ለዘላቂ ሰላምና መረጋጋት፥ ለቋሚና ዘላቂ የዴሞክራሲ ሥርዓተ መንግሥት መመስረት፥ በግድ ወያኔን ማስወገድና የሀገሪቱን ዜጎች ሁሉ የሚያሳትፍ ብሔራዊ አውደ-መድረክ አስፈላጊና ወሳኝ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ፥ የወያኔን ፃዕረ ሞት፥ እስትንፋስ ለመስጠትና አሁን ያለው ሁኔታ እንዲቀጥል የሚደረገው ብልጣ ብልጥነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ካለማግኘቱም በላይ፥ ጊዜው ያለፈበት ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው።  አግላይነትና የጥሎ ማለፍ የፖለቲካ ጨዋታ*

*በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ለገባቸው ኢትዮጵያ ፈጽሞ አይሰራም።*

*ታሪክ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ እራሱን የመደጋገም ባኅርይ ሊኖረው ቢችልም፥ በደርግ አመጣጥ ወቅት የሆነው ክስተት መልኩን እየለዋወጠ እንደገና ዛሬ በአዲስ አጋጣሚ ብቅ ማለቱ ደግሞ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያስገረመውና እያስደነቀው በመሄድ ላይ ይገኛል። ከዛሬ ሠላሳ ዓመታት በፊት፥ ለደርግ ሂሳዊ ድጋፍ እየሰጠን ዐብዮቱን መምራት እንችላለን ብለው የመጡ ቡድኖች፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሔራዊ ዓብዮታዊ ትግል ለፋሽስቶች አጋልጠው በመስጠት የሆነውን ሁሉ መለስ ብሎ ሲመለከት፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቅርብ ጊዜ መራራ ትዝታ ነው። ከዚህ መራራ ታሪክ ያልተማሩ ክፍሎች ዛሬም እንደ ትላንቱ፥ በወያኔ ስር እየተገዙ በመታገል ሀገርን ማዳን ይቻላል በሚል አሳፋሪ አቅዋም ሽፋን፥ እየተሰባሰቡ ይገኛል። የትላንትናዎቹ ቡድኖች ሂሳዊ ድጋፍ እንስጥ ብለው በፋሽቱ ደርግ ምን እንደደረሰባቸው ሁሉም የሚያውቀው በመሆኑ ወደዝርዝር መግባቱ አስፈላጊ ባይሆንም፥ የዛሬዎቹ ደግሞ ከነመለስ ጋር ለመተባበር በሚያደርጉት መሰናዶ የሚሰጡት ማጠየቂያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ለማኮላሸት ይጥራሉ። ለእጅ መንሻ ይጠቅመናል የሚሉትን ማነኛውንም ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን እየታዘበ የሚገኘው ኅብረትሰብም እንደማይታለል ግን የተረዱት አይመስልም። ከወያኔ ጋር ለመጠጋት በሚያደርጉት ጭንቀት፥ "ጀግናው ሠራዊታችን" የሚል የታማኝነት መግለጫ በማሰማት የመኅንበሻ ምዕራፍ ከፍተዋል። ወያኔን እንርዳ ብለው ታሪክን ለመበረዝ የጣሩ ግለሰቦች፥ ቀደም ሲል "ፎረም 84" የሚል ለምድ በመልበስ ቢሞክሩም፥ ወያኔ ለጥቂት ጊዜ ከተጠቀመባቸው በኋላ አንቅሮ እንደተፋቸው፥ ሌላው ቢቀር ለአዲስ አበባ ነዋሪ የቅርብ ትዝታ ነው። ታምራት ላይኔ ራሱስ ዛሬ የት ነው? በማነኛውም ኅብረተስብ ውስጥ በየአንዳንዱ አስራ ሁለት ሐዋርያት አንድ ይሁዳ እንደማይጠፋ የኢትዮጵያ ሕዝብ አበክሮ ስለሚያውቅ፥ ምርጫውን በዕምነታቸው ፀንተው ከሚታገሉት ጋር አዋኅዶ ለዴሞክራሲና ለሀገር አንድነት የሚያደርገውን ትግል እንደሚያጧጡፈው አንዳችም ብዥታ ሊኖር አይችልም።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛ ጥያቄው፥ ዓላማውና ራዕዩ ፥ ከወያኔ ኅልፈት በኋላ የሀገሩ ዕድል ምን ይሆናል? ተተኪው ማን ነው? ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ሊያመጣ የሚችለውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዴት ዕውን ሊሆን ይችላል? ወያኔ ዘርቶት የሚሄደውን የዘረኝነት በሽታ እንደምን አድርገን መፈወስ እንችላለን? ዛሬ ሀገራችንን ያጥለቀለቃትን በሽታ፥ ድኅነት፤ ረሀብ፥ የኢኮኖሚ ድቀት፥ ሥራፈትነት፥፥ ስደት፥ እስራት፥ ብሔራዊ ውርደትና ጥቃት፥ በምን ኃይልና ጥበብ ማስወገድ እንችላለን? የሚለው ነው።*

*በእኛ ዕምነት፥ እነኝህንና የመሳሰሉትን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ የሚቻለው፥ የሀገሪቱን ዜጎች በሞላ የሚያሳትፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲመሠረት ብቻ ነው እንላለን። ይህን ዕውን ለማድረግ ደግሞ፥*

በቅድሚያ አንድ የሽግግር ወቅት እንዲኖር ግድ ይላል። በሽግግሩ ወቅት እከሌ ከእከሌ ሳይለይ ማነኛውም የፖለቲካ፥ የማኅበረሰብና የዜጎች ተወካዮች የሚሳተፉበት ብሔራዊ የሠላምና ዕርቅ ጉባዔ መጠራት አንገብጋቢና አስፈለጊ መሆኑን ሁሉም ሊያምንበት ይገባል። በተጨማሪም፥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀዳሚ ፍላጎቱና አጀንዳው፥ ከወያኔ ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት መላቀቅ ብቻ ሳይሆን፥ ዳግመኛ እንደነ ወያኔ ዓይነት ቡድን፥ እራሱን አዋርዶ ሀገርን የሚያዋርድ ሌላ አምባገነን እንዳይተካበትም ጭምር ነው። ከወያኔ መሪዎች የበለጠ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላት አልነበረም ለማለት ቢቻልም፥ የባሰ አታምጣ ተብሎ እየተዋረዱ መኖር ደግሞ፥ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ ሊሆን ከቶ አይገባውም። በመሆኑም፡ ይህ ዘረኛ ሥርዓት በአስቸኳይ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት ይዋል ይደር የሚባል ተልዕኮ አይደለም። እያንዳንዱ ትውልድ የየራሱን አኩሪ ተግባር እየፈጸመ፥ ለተተኪው ትውልድ እያስረከበ ማለፍ አለበት። ይህን ለማድረግ ደግሞ፥ የዓላማ ፅናትን፥ የቃል ኪዳን አክብሮትን፥ ለአምባገነን ሥርዓት አይበገሬነትን፥ የሀገርን ብሄራዊ ጥቅምን ለአላፊ ጠፊ የሥልጣን ፍርፋሪ አለመለወጥን፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊነት ማመንን ይጠይቃል። ታሪክ እየሰሩ በታሪክ ፀጋ ተከፍኖ፥ በአኩሪ ታሪክ ሐውልት ስር መቀበር፥ የቆራጥ ኢትዮጵያውያን ታጋዮች በተለይ የተሰጠ ዕድና ፀጋ እንጅ፥ ለማንም ተንበርካኪ የሚታደል አይደለም። በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከአ-ምድር ውስጥ ዕድሜ ላደለው ዜጋ ፥ ጎራው እየለየ፥ ማንነት እየተያ መጥራቱን መታዘብ ይችላል።///////////////